## የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)
## ስለ ተማሪ የጾታ መለያ ጉዳዮች መመሪያ[1]

የጾታ ጉዳዮችን በተመለከተ እያንዳንዱ ሠራተኛ እና ተማሪዎች እውቅና መስጠት እና ማክበር ያለባቸው የጾታ መለያ ጾታ የቀየሩ ተማሪዎችን ጨምሮ ወይም ያልተረጋገጠ ጾታ፣ እናም እንደዚህ ዓይነት ተማሪዎች በደስታ የጾታ ምንነታቸውን ገልጸው ለመናገር ነፃነት እንዲሰማቸው። በተቻለ መጠን፣ በሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የጾታ ማንነት ጥያቄዎችን መቀበል/ማስተናገድ እና የተማሪዎችን ግላዊ ማንነት ምስጢር መጠበቅ/መከላከል የሚተገበር ነው። MCPS፤ ተማሪዎች በትምህርት እንዲጠመዱ እና ከት/ቤት ማህበረሰብ ጋር ተቀባይነት እንዳላቸው ተሰምቷቸው በንቃት እንዲሳተፉ ለሚያጓጓና ሰላማዊ የትምህርት ቤት አካባቢ ለማራመድ ቁርጠኝነት አለው። በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ዋና እሴት መሠረት፣ የሚከተሉት መመሪያዎች ከሜሪላንድ የስቴት ትምህርት መምሪያ መመሪያዎችም ጋር የሚጣጣሙ [2] እና ከትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA, አድሎ የሌለበት፣ ፍትህ/እኩልነት፣ እና የጎለበተ ባህል[6]፣በመላ ስርአትአቀፍ ደረጃ፣ አድሎአዊነት፣ ማግለል/በሰው ላይ መጠቋቆም፣ እና ማስፈራራት/ጥቃት ተቀባይነት አይኖረውም። በዚህ መመሪያ ሊሆን የሚችል እያንዳንዱን ክስተት ሁሉ ለመተንበይ አይቻልም። ስለዚህ/በዚህ ምክንያት፣ የእያንዳንዱ/ዷ ተማሪ ፍላጎት መታየት ያለበት አንድ-በ-አንድ/እንደጉዳዩ ሁኔታ ነው።

ግቦች

- ተማሪዎች ከጾታዊ ማንነታቸዉ ጋር ከሚጣጣም በትምህርት ቤት ህይወት ለመሳተፍ እንዲችሉ መርዳት፤
- የጾታ መገለጫቸውን እንዲጠብቁና እና ጾታ የቀየሩት የግል አቋማቸው በሚስጥር እንዲያዝ የተማሪዎችን መብት ማክበር።
- ጾታቸውን በቀየሩት ላይ እና ሥርዓተ-ፆታን በማያሟሉ ተማሪዎች ላይ የሚደረግ የማግለል/የመጠቋቆም፣ እና ዝቅ አድርጎ የማየትን ሁኔታ መቀነስ፣
- ጾታቸውን የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን የማያሟሉ ተማሪዎችን ማህበራዊ ዉህደት እና በአብሮነት የማቀፍ ባህልን ማሳደግ/ማበረታታት፤ እና
- ስለተማሪዎች የጾታ ማንነት ጉዳይ እውቀት እንዲኖራቸውና በአግባብ እና በቀጣይነት ለመርዳት እንዲችሉ ሠራተኞችን ማገዝ።

ትርጉም

እዚህ የተሰጡት ትርጉሞች ተማሪዎችን ለመፈረጅ ታስቦ ሳይሆን ነገር ግን ጾታቸውን የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን የማያሟሉ ተማሪዎችን በመረዳት ድጋፍ ለመስጠት እንዲያስችል ነው። ተማሪዎቹ ስለ ራሳቸው ለመግለጽ ይህንን ቃላት/ፍቺ ይጠቀሙ/አይጠቀሙ ይሆናል።[3]

- ጾታ-ያልተለየ/ጾታ አልባ፡- ጾታ-አልባ (ጾታው(ዋ) ያልተለየ፣ጾታ-የለሽ)።
- በልደት ጊዜ የተሰየመ ጾታ፡- በሕፃንነት የልደት ሠርተፊኬት ላይ የተመዘገበው የጾታ መገለጫ-በተወለደ(ች)በት ወቅት ተመዝግቦ ከሆነ።
- የጾታ ማንነት፣ መለያ፡- ሰው ስለራሱ/ሷ ጾታ በጥልቀት የሚሰማው ስሜት ወይም ስነልቡናዊ/ሳይኮሎጂያዊ እውቀት/አስተሳሰብ። የአንድ ሰው የጾታ መገለጫ በትውልድ ከተሰጠው/ከተሰጣት የጾታ ማንነት ጋር አንድ ዓይነት ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች በተወለዱ ጊዜ ከተሰየሙት የጾታ መለያ/ማንነት ጋር የሚገጣጠም የጾታ መገለጫ አላቸው። ቢሆንም እንኳ፣ ለአንዳንዶች፣ የፆታ ማንነታቸው በተወለዱበት ጊዜ ከተሰየመላቸው የፆታ መለያ የተለየ ነው። ሁሉም ሰው የፆታ መለያ አለው፣ ፆታቸውን የቀየሩ ሰዎች ብቻ አይደሉም። ለዚህ መመሪያ ዓላማ፣ የአንድ ተማሪ ፆታው(ዋ) በት/ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በይፋ የታወቀ/የተረጋገጠው ነው።
- የፆታ መገለጫ፡- አንድ ሰው/አንዲት ሴት ጾታው(ዋ)ን ለሌሎች የሚገልጽበት/የምትገልጽበት ሁኔታ/ዓይነት/አኳሀን፣ አብዛኛውን

---

[1] ተዛማጅ የሆኑ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንቦች፡- ACA, ACF, JHF, JHF-RA, ACA-RA, ACF-RA

[2] የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለተጨማሪ ምንጭ፣ ይመልከቱ፡- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ ጾታ የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን ላላሟሉ ወጣቶች ሰላማዊ/የማያሰጋ ስፍራ መስጠት፡- በጾታ ማንነት ምክንያት አድሎ እንደማይደረግ መመሪያ (ኦክቶበር 2015)፣ በ ይገኛል፤ marylandpublicschools.org/about/Documents/DSFSS/SSSP/ProvidingSafeSpacesTransgendergenderNonConformingYouth012016.pdf.

[3] ፍቺዎቹ የተገኙት ከሚከተሉት ምንጮች አማካይነት ነው፡- American Psychological Association; Maryland State Department of Education; Maryland Public Secondary Schools Athletic Association; National School Boards Association; National Collegiate Athletic Association; Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education; New York City Department of Education; California School Boards Association; Howard County Public Schools; District of Columbia Public Schools; Chicago Public Schools; Gay, Lesbian & Straight Education Network; Lambda Legal; and American Civil Liberties Union.

ጊዜ በባህርይ፣ በአለባበስ፣ በፀጉር አያያዝ፣ በእንቅስቃሴዎች፣ በድምፅ፣ በንግግር እና በቃላት አመራረጥ፣ ወይም ልዩ ጠባይ/ዘይቤ ነዉ።

- *ጾታን መቀየር*:- ሰው በተወለደ(ች)በት ጊዜ ከተሰየመለ(ላ)ት ፆታ በተለምዶ ከሚታወቅበት/ከምትታወቅበት የተለየ የፆታ መገለጫ ቅፅል ነው። *ተመሣሣይ ትርጉም የሚኖራቸው ሌሎች ቃሎች* " ቅይር ሴት/ወንድ transsexual (ሴት ነኝ ብሎ የሚያምን ወንድ/ወንድ ነኝ ብላ የምታምን ሴት-- በቀዶ ጥገና ፆታውን ያስቀየረ/ያስቀየረች) " እና " ቅይር/trans "
- *ሥርዓተ-ፆታ የማያሟሉ/የማያሳዩ* :- በተለምዶ ከሚታወቀው ወይም ከጅምላ አመለካከት የፆታ አገላለጽ በተለይ የሚጠበቅ፣ እንደ "ሴታሴት" ወንዶች፣ "ወንዳወንድ" ሴቶች፣ እና ሌሎች የፆታቸው አገላለጽ ውህደፆታ (የሁለቱንም ፆታ መራቢያ ይዞ የተፈጠረ ሰው) የሆነ። ይህ የሚያካትተው በተለምዶ ከሚታወቀው ዓይነት የፆታ አገላለጽ ስያሜ ውጪ ወይም እንደ ሁለት ወይም የበለጠ (የተለየ) ፆታዊ ማንነት እንዳላቸው የሚገልፁትን ነው። ሌሎች በተመሣሣይ ትርጉሞች የሚካተቱ "ልዩ ልዩ ፆታ" ወይም "ፆታን ማስፋፋት" የተባሉትን ቃላት ይሆናል።
- *ሽግግር*:- ከፆታዊ ማንነቱ/ቷ ጋር ለማገጣጠም የፆታ አገላለጽን የመቀየር ሂደት/አካሄድ። የፆታ ማንነታቸውን ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽ እንዲያመቻቸው፣ ፆታቸውን ያስቀየሩ ሰዎች የተለያዩ ደረጃዎችን ይወስዱ ይሆናል (ለምሳሌ:-ቅጽል ስም መጠቀም ወይም ስማቸውን በህጋዊነት መቀየር እና/ወይም የተሰየሙበትን ፆታ በህጋዊ ሠነዶቻቸው ሁሉ ላይ ማስቀየር፣ አለባበስ እና የፀጉር አያያዛቸውን የመረጡትን ፆታ ማንነት እንደሚያንፀባርቅ አርገው መቀየር እና አጠቃላይ አኗኗራቸውን፣ እና ለሌሎች ራሳቸውን የሚያሳውቁበት ሁኔታ፣ ከፆታ ማንነታቸው/መለያቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ይሆናል)። ጥቂቶች፣ ነገር ግን ሁሉም አይሆኑም፣ ፆታቸውን የሚቀይሩ ሰዎች እድገ-ንጥር/ሆርሞን/ መድኃኒት ይወስዳሉ ወይም በቀዶ ጥገና ህክምና ተለውጦ ሰውነታቸው ከፆታ ማንነታቸው ጋር እንዲመሣሰል ያስደርጋሉ።
- *የተፈጥሮ ፆታው(ዋ)ን የያዘ(ች)/Cisgender*:- ሲወለድ/ስትወለድ የያዘውን/የያዘችውን ፆታ ጠብቆ(ቃ) ያለ(ች) ፤ፆታ ያልቀየረ(ች) ወይም ሥርዓተ ፆታን የማያ(ታ)ሟላ/የማይታይበ(ባ)ት።

*ፆታ ከቀየሩ እና ሥርዓተ ፆታ ከማያሟሉ/ከማይታይባቸዉ ተማሪዎች ጋር በንቃት መሥራት*

- ርእሰ መምህር/ት (ወይም ተወካይ) ከተማሪ እና ከተማሪ ቤተሰብ ጋር በመተባበር (ቤተሰብ ተማሪው(ዋ)ን የሚደግፉ ከሆነ)፣ ተማሪው(ዋ) በት/ቤት እንቅስቃሴዎችና በሁሉም ፕሮግራሞች ላይ እኩል የመሣተፍ እድል እንዲኖረው/እንዲኖራት እናም ከፆታ ነክ የማግለል አድሎአዊ ሁኔታ ጥበቃ/ከለላ እንደሚደረግላቸው እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው። ት/ቤቶች የ MCPS ቅጽ 560-80 መጠቀም አለባቸው። *የመቀበያ ቅጽ:- የተማሪ ፆታ ማንነት/መለያ መደገፍ* (አባሪ A-1)ይህንን ሂደት ለመደገፍ
- የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አንድ-በአንድ መገምገም አለበት፣ እና ሁሉም እቅድ በሂደት እየተገመገመ እንደአስፈላጊነቱ ይከለሳል። ት/ቤቶች አንድ ቁልፍ የሆነ/ች ተማሪዎች የሚገናኙ/ኟት ሰው(ሰዎች) የእቅዳቸው አካል አድርገው መመደብ አለባቸው። እቅዱ እንዴት ድጋፍ እንደሚሰጥ፣ እንዴትና ለማን ኢንፎርሜሽን መነገር እንዳለበት በእቅዱ ላይ መገለጽ/መታየት/መነደፍ አለበት። በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ እቅድ የተመረጠውን ስም፣ እና አጠራር፣ አትሌቲክስ፣ ከቀለም ትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎችን፣ መቆለፊያ ክፍሎች፣ መፀዳጃ ክፍሎች፣ ሰላማዊ ስፍራዎችን፣ የተከለሉ ቦታዎች/ዞን እና ሌሎች የሰላም ድጋፎች፣ እና እንደ የተማሪዎች መመረቂያ ፕሮግራም ዓይነት መደበኛ ክንውኖችን ማካተት አለበት።
- ርእሰ መምህሩ/ሯ ወይም የተመደበው ሰው ከወላጅ/ሞግዚት ጋር ከመነጋገራቸው አስቀድመው፣ ከቤት ምን ያህል ድጋፍ እንዳለው/እንዳላት ወይም ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚጠብቅ/እንደምትጠብቅ ለማረጋገጥ ከተማሪው(ዋ) ጋር መነጋገር አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ፆታቸውን የቀየሩ እና ሥርዓተ-ፆታን የማያሟሉ/የማያሳዩ ተማሪዎች ሰላም እንዳያጡ ወይም ተቀባይነት አይኖረኝም በሚል ስጋት ምናልባት እቤታቸው ውስጥ የጾታ መለያቸውን በግልጽ አይናገሩም ይሆናል። የፆታ ማንነት/መለያ ጉዳይ ውስብስብ ሊሆንና የቤተሰብ መበጣበጥን ሊያስከትል ይችላል፣ ጉዳዩ እንደዚህ ከሆነና ድጋፍ መስጠት የሚያስፈልግ ከሆነ፣ የት/ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ወይም የተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤትን (OSFSE) ማነጋገር/ማግኘት ያስፈልጋል።

ስለ ግል ገመና እና ኢንፎርሜሽን መስጠት

- *ሁሉም ተማሪዎች ስለግል ገመናቸው መብት አላቸው።* በት/ቤት ውስጥ ይህ የሚያካትተው የአንድን ሰው ፆታ የመቀየር አቋም ወይም ሥርዓተ -ፆታ ያለማሟላት አቀራረብ የግል መብትን ጭምር ነው።
- ስለ አንድ ተማሪ የፆታ መቀየር አቋም፣ ህጋዊ ስም፣ ወይም በተወለደ(ች) ጊዜ የተሰጠ ፆታ ከህክምና ጋር የሚገናኝ ሚስጥራዊ መረጃ ሊሆን ይችላል። ይህን ዓይነት መረጃ ለሌሎች ተማሪዎች መግለጥ፣ ወይም ለወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው፣ ወይም ለሦስተኛ ወገን ማጋለጥ የግል ገመናን ህግ እንደ ፌደራል "የቤተሰብ የትምህርት መብት እና የግል ገመና ደንብ" (FERPA) መጣስ ይሆናል።
- *ፆታ ከቀየሩ ተማሪዎች ጋር የሚገናኙ የህክምና መረጃዎች በጠቅላላ በስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌደራል ህጎች የግል ገመና ስለ መጠበቅ ደንቦች አግባብ መሠረት በሚስጥር መጠበቃቸውን ት/ቤቶች ማረጋገጥ አለባቸው።*
- እባክዎ ያስታውሱ የህክምና ምርመራ፣ ህክምና የተደረገበት ወይም ሌላ አይነት ማስረጃዎችአስፈላጊ አይደለምት/ቤት ስለ ፆታ ማንነት የሚቀርብ ጥያቄ ለመቀበል/ለማስተናገድ

- *ፆታ ያስቀየሩ እና ሥርዓተ - ፆታ የማያሟሉ ተማሪዎች ስለ ፆታ ማንነታቸው ውይይት ለማድረግ፣ ስለፆታቸው እንዲታወቅላቸው ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እና በግልጽ መቼ፣ ከማን ጋር፣ እና የግል ገመናቸውን ምን ያክል ማሳወቅ እንዳለባቸው ለመወሰን መብት አላቸው። ተማሪዎቹ አቋማቸውን ለሥራ ባልደረባ በመግለፃቸው ወይም ለሌሎች ተማሪዎች አሳወቁ ማለት የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ቤተሰቦችን/አሳዳጊዎችን እና የት/ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ ለሌሎች ስለተማሪዎቹ አቋም እንዲገልጹ ተፈቅዷል ማለት አይደለም። ተማሪዎቹ ራሳቸው ፈቅደውላቸው ካልሆነ ወይም በህግ ተጠይቆ ካልሆነ በስተቀር።*

*ስሞች/ተውላጠ ስሞች*

- *የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ተማሪዎችን መጥራት ያለባቸው በት/ቤት ውስጥ ዘወትር በሚጠሩበትና ከፆታ ማንነታቸው ጋር በሚገጣጠም የተረጋገጠ ስም/ተውላጠስም መሆን አለበት። ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር የሚመሳሰል/የሚጎዳኝ የስም፣ እና/ወይም የጾታ ለውጥ፣ ስለማድረጋቸው ወይም የተማሪ ሪኮርድ/መረጃዎችን ስለማስቀየር እንደቅድመሁኔታ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ማግኘት አይጠበቅባቸውም። በተቻለ መጠን፣ እና ከዚህ መመሪያ ጋር በማጣጣም የት/ቤት ሠራተኞች ፆታ የቀየሩ ተማሪዎችን አቋም/ገመና በሚስጥር ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ አለባቸው።*
- *ምንጊዜም ት/ቤቶች የተማሪን የልደት ህጋዊ የመጠሪያ ስም ወይም ፆታ በት/ቤት መዛግብቶች/ፋይሎች እና በሌሎች ሠነዶች ላይ እንዲጠቀሙ በህጋዊ ካልተጠየቁ በስተቀር ት/ቤቶች ለክፍል ስም መጥሪያ መዝገብ፣ የመታወቂያ ባጅ፣ ለማስታወቂያዎች፣ ለሠርተፊኬቶች፣ ለጋዜጦች፣ እና ለዓመታዊ መጽሔት ጭምር በተማሪው/ዋ የተመረጠውን ስም እና ፆታ መጠቀም አለባቸው።*

*ይፋዊ መዛግብት/ፋይሎች*

- *ት/ቤቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ ህጋዊ ስም እና ፆታ የሚገልጽ ቋሚ የሆነ ፋይል/መዝገብ ሊኖራቸው ይገባል። ት/ቤቶች በተማሪ ቋሚ መዝገብ/ፋይል ላይ ያለ ስም እና ፆታ እንዲጠቀሙ በሚያስፈልግ ሁኔታ፣ ለምሳሌ :-ደረጃ የጠበቁ ቴስት/ፈተናዎች፣ ወይም ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ሪፖርቶች፣ የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች እና አስተዳዳሪዎች ባለማስተዋል/በመዘናጋት ተማሪው/ዋ የመረጠ(ች)ውን ህጋዊ ስም እና ፆታ ጋር ተመሣሣይ ያልሆነ ነገር እንዳያስተላልፉ ልምምድ ማድረግ አለባቸው።*
- *የተማሪ ቋሚ ፋይል/ማህደር ለውጥ በተደረገው ህጋዊ ስም ወይም ፆታ ለውጥ ስለመደረጉ በሚያረጋግጠው የፍርድ ቤት ትእዛዝ ሠነድ/መረጃ፣ አዲስ የልደት ሠርተፊኬት፣ በስቴት ወይም ፌዴራል አማካይነት የተሰጠ መታወቂያ፣ ወይም ፈቃድ ካለው ኃኪም በሚቀርብ ማስረጃ መሠረት መቀየር አለበት። ተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ እነዚህ ማስረጃዎች ሳይኖሩ የተማሪው ህጋዊ ፋይል እንዲቀየር ከጠየቁ ት/ቤቱ OSFSE ን መጠየቅ አለበት።*
- *ስለ ተማሪው/ዋ ህጋዊ ስም እና/ወይም ፆታ ለውጥ ከተደረገ በኋላ ት/ቤቱ የቀድሞውን የተማሪው(ዋ)ን ቀደምት ማንነት ለመጠበቅ መፍትሔ መስጠት አለበት፣ ቀደም ሲል የነበሩት መዛግብት/ፋይሎች/ሪኮርዶች የማይመለከታቸው የት/ቤት ሠራተኞች በቀላሉ በማይደረስበት/ለማየት በማይችሉበት ቦታ መጠበቅ አለበት።*
- *በተማሪው፣ ወይም በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት አረጋግጠው ካልሆነ በስተቀር፣ የት/ቤት ሠራተኞች ፆታ የቀየረ/ች ተማሪን ወላጅ/ሞግዚት በሚያገኙበት ጊዜ ተማሪው/ዋ በተወለደ(ች)በት ወቅት ከተሰየመው ፆታ ጋር የሚጣጣመውን ህጋዊ ስም እና ተውላጠ ስም መጠቀም አለባቸው።*

*የአለባበስ ደንብ/ሥርዓት*

- *ፆታ የቀየሩ እና ሥርዓተ ፆታ የማያሟሉ ተማሪዎች ከ MCPS የአለባበስ ደንብ/ሥርዓት ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ ከፆታ መለያቸው ወይም አገላለፃቸው ጋር በሚስማማ ዓይነት የመልበስ መብት አላቸው። የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ሌሎች ተማሪዎች ላይ ከሚያደርጉት የበለጠ አለባበስን በሚመለከት ፆታቸውን የቀየሩ ወይም ሥርዓተ ፆታ በማያሟሉ ተማሪዎች ላይ ተጽኖ ማድረግ አይኖርባቸውም።*
- *ለክፍል ወይም ዓመታዊ መጽሐፍ/መጽሔት ፎቶ፣ የላቀ ትምህርት ለሚማሩ ማህበረሰብ በዓላት፣ ለምረቃ በዓላት፣ ወይም የዳንስ ዝግጅቶች ሲኖሩ ት/ቤቶች ጾታዊ አለባበስን የማይመለከት (gender neutral dress codes) የአለባበስ ሥርዓት መከተል አለባቸው።*

*ፆታን-መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች*

- *ት/ቤቶች በጠቅላላ በፆታ ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን፣ ህጎች/ደንቦችን እና አሠራሮችን መገምገም እና ከስነ ማስተማር ጋር የተያያዙ ግልጽ እና ትርጉም ያላቸው ላይ ማተኮር/መጠበቅ አለባቸው። በት/ቤት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ላይ በፆታ እንዲለያዩ ሲፈለግ ወይም በሌላ ህጋዊነት ባላቸው ፆታን የሚመለከቱ ህጎች/ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ አፈፃፀም፣ ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት።*

*ፆታ-ያሚለይባቸው አካባቢዎች*

- መገልገያዎች በፆታ ተለይተው ለተማሪዎች ሲመደቡበፆታ ተለይቶ የሚመደብ መገልገያዎችን እንዲጠቀሙ መሰጠት አለበት (ለምሳሌ:- መፀዳጃ ቤቶች፣ እቃ መቆለፊያ ክፍሎች፣ እና ልብስ መቀየሪያ ክፍሎች) ከተረጋገጠው ፆታ መለያቸው ጋር የሚጣጣም በሆነ መልኩ
- ማንኛውም ተማሪ ለደንነቱ/ቷ፣ ግላዊ ሁኔታ፣ ወይም በሌላ ምክንያት፣ የጋራ መገልገያዎችን ለመጠቀም ስጋት ካለበ(ባ)ት፣ ጥያቄ ካቀረበ(ች) አስተማማኝ/የማያሰጋ እና እፍረት የማይሰማቸውና የማይሸማቀቁበት (ሌሎች የማይጠቋቆሙባቸው ስፍራ) አማራጭ ለምሳሌ:- የብቻ መታጠቢያ ክፍል፣ ወይም መቆለፊያ ክፍሎችን በሚመለከት፣ መከለያ ወይም መጋረጃ ያለው ልብስ መቀየሪያ አካባቢዎች፣ በቅርብ ያለ መፀዳጃ ክፍል ወይም ቢሮ፣ ወይም የተለየ ልብስ መቀየሪያ መርሃግብር አማራጭ መሰጠት አለበት። ተማሪው/ዋ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መደረግ ያለበት ሚስጥራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።
- በፆታ አምሳያነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ለሚችሉ ተማሪዎች ሌላ አማራጭ እንዲዘጋጅላቸው አያስፈልግም። አማራጭ ሁኔታ ለመጠቀም በተማሪው/ዋ ጥያቄና የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ግላዊ ሚስጥር ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ነው።
- አንዳንድ ተማሪዎች በፆታ ተለይቶ የተመደበ መገልገያ ፆታው(ዋ)ን ከቀየረ/ች ተማሪ ጋር ለመጠቀም አይመቻቸውም ይሆናል። ይሄ ያለመመቸት ፆታው(ዋ)ን ለቀየረ/ች ተማሪ እንዳይ(ት)ጠቀምበት ለመከልከል ምክንያት ሊሆን አይችልም። የት/ቤት አስተዳዳሪዎች እና አማካሪ የሥራ ባልደረቦች ስለ ፆታ መለያ/ማንነት እንዲገባቸው ለማስረዳት እና ለሁሉም ተማሪዎች መከባበርና ዋጋ መስጠትን በማዳበር የማይመች ሁኔታን ለመቀየር ከተማሪዎች ጋር መሥራት አለባቸው።
- አዲስ ግንባታ/እድሳት:-
    - የት/ቤት አስተዳደር በአገልግሎት ላይ የሚገኙት ህንፃዎች ለገለልተኛ-ፆታ አገልግሎት እንዲውሉ ለማድረግ አመቺነት ከሌላቸው ት/ቤቶች ከአገልግሎት መሣሪያዎች ማደራጃ ክፍል ጋር በመሆን ስልመገልገያዎች እቅድ እና ያሉትን መገልገያዎች እድሳት ጭምር በጋራ መሥራት አለበት።
    - የተማሪን ደህንነት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የአገልግሎት መሣሪያዎች ማደራጃ ክፍል በፆታ-ያልተገደበ ለተማሪ/ለህዝብ መገልገያ የሚሆን መፀዳጃ ለመሥራት ንድፍ ማዘጋጀት አለበት።
    - አስፈላጊነቱ ከታመነበት፣ MCPS በእያንዳንዱ ደረጃ-ፎቅ/ፍሎር እና ሰው በሚበዛበት አካባቢ ቢያንስ አንድ ፆታ-ገለልተኛ ሽንት ቤት መሰራት አለበት።
    - በተቻለ መጠን፣ MCPS አዲስ በሚሰሩ እና እድሳት በሚደረግላቸው የት/ቤት ህንፃዎች ሰላማዊ-ለደህንነት የማያሰጋ፣ ግላዊ ገመናን የማያጋልጥ እና የቦታውን አመቺነት ግምት ውስጥ በማስገባት ቢያንስ አንድ ፆታ-ገለልተኛ ልብስ መቀየሪያ እንዲጨመር መደረግ አለበት።

የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት እና በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ ስፖርት

- ምንጊዜም ት/ቤት በጾታ-የተለየ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ሲሰጥ እና በት/ቤቶች መካከል ባሉ ስፖርቶች፣ ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር በሚመጥን ስፖርት እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚካሄድ አትሌቲክስ

- በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚካሄድ አትሌቲክስ የተማሪ ተሳትፎ የሚወሰነው በሜሪላንድ የሕዝብ ት/ቤቶች የአትሌቲክስ ማህበር (MPSSAA) ፖሊሲ እና መመሪያ መሠረት ነው።
- በ MPSSAA መመሪያ እና የውድድር ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ፣ የሴቶችንም ስፖርቶች ልዩነት/አድሎ ሳይደረግ በአንድነት ተፎካካሪነት እንዲሳተፉ እኩል እድል ለመስጠት፣ ፆታቸውን ያስቀየሩ እና ሥርዓተ -ፆታን የማያሟሉ ተማሪዎች በ MCPS የት/ቤቶች አትሌቲክስ ላይ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት። (ሀ) ተማሪው/ዋ በትውልድ የተሰየመ ጾታ፣ (ለ) ተማሪው/ዋ ያስቀየረው/ያስቀየረችው ፆታ፣ (ሐ) በትምህርት ቤት ተመዝግቦ የሚገኘው የተማሪው/ዋ ፆታ መለያ (ህጋዊ ስም እና ፆታ ለመጠበቅ በሕግ የተደነገጉትን መዝገቦችን አይጨምርም)።
- ማናቸውንም የት/ቤቶችን አትሌቲክስ በሚመለከት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ት/ቤቶች ለ MCPS አትሌቲክስ ክፍል ማስተላለፍ አለባቸው።
- በሌሎች ት/ቤቶች የሚካሄዱ ውድድሮች፡ ተማሪው/ዋ በሚማርበት/በምትማርበት ት/ቤት የተዘጋጀለ(ላ)ት መገልገያዎች በሌሎቹም ት/ቤቶች እንደሚገኝ ከተማሪው/ዋ ጋር በመነጋገር የተማሪው/ዋ እቅድ አካል ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል። ኮች/አሰልጣኝ ወይም ተማሪው/ዋ የሚ(ምት)ማርበት ት/ቤት በሌላኛው ት/ቤት አስፈላጊ ነገሮች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ እንዲ(ድት)ገበኝ መጠየቅ ያስፈልጋል፣ የተማሪው/ዋ ማንነት በሚስጥር እንደተጠበቀ ሆኖ።

ከክፍል ውጭ ትምህርት/በምሽት የመስክ ጉዞዎች

- ተማሪዎች ባረጋገጡት የፆታ መለያቸው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ እንዲሳተፉ መፈቀድ አለበት።

- ስለመኝታ ቦታ/ሁኔታ ዝግጅት ከተማሪው/ዋ እና ከቤተሰብ (ቤተሰብ ተማሪውን/ተማሪዋን የሚደግፍ ከሆነ) ጋር መወያየት ያስፈልጋል። ከተጠየቀ፣ ለተማሪው/ዋ ሌሎች የማያሾፉበትና የማያሸማቅቁበት ሰላማዊ ቦታ እንደአማራጭ መዘጋጀት አለበት ለምሳሌ ከተቻለ ለብቻ ለመተኛት የሚመች አካባቢ
- ት/ቤቶች ማናቸውንም የግል ገበና ለመጠበቅ የሚፈልግ/የምትፈልግ ተማሪ ፣ በተቻለ መጠን ፣ ከሌሎች ተማሪዎች ባለማግለል ለማስተናገድ መሞከር አለባቸው።
- የተማሪው(ዋ) ፆታ የመቀየር አቋም በሚስጥር የሚጠበቅ ኢንፎርሜሽን ስለሆነ የት/ቤት ሠራተኞች ማጋለጥ የለባቸውም ወይም ለሌሎች ተማሪዎች ለወላጆቻቸው/ለአሳዳጊዎች ከመስከ ጉዞ ጋር በተገናኘ ምክንያት ተማሪው/ዋ ሳያ(ታ)ውቅ እና/ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ሳይስማማ የተማሪው(ዋ)ን ፆታ የመቀየር ሁኔታ ማጋለጥ የለባቸውም።

ወከባ/ማስፈራራት እና ትንኮሳ/ማስጨነቅ

- የMCPS ቦርድ ፖሊሲ JHF እና የMCPS ደንብ JHF-RA ስለ ወከባ-ማስፈራራት እና ትንኮሳ-ማስጨነቅ፣ በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/section.aspx?sectionID=10.
- ወከባ-ማስፈራራት እና ትንኮሳ-ማስጨነቅ የሚያካትተው በተማሪው(ዋ) ላይ ያተኮረ ነባራዊ ወይም በግምታዊ አስተሳሰብ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ እና ተማሪው(ዋ) በሚቀርበው/በምትቀርበው ጓደኛ ባህርይ፣ የቤተሰብ አባል፣ ወይም ሌላ ሰው ወይም ቡድን በተማሪው(ዋ) ላይ ያነጣጠረ ባህርይን ነው።
- በነባራዊ ሁኔታ ወይም በይሆናል በተማሪ የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪ ላይ ያነጣጠረ ማስጨነቅ፣ ወከባ፣ እና ማስፈራራት፣ ልዩነት/አድሎ የማድረግ ቅሬታ ሲቀርብ እንደሌሎቹ አድሎአዊነትን የማስወገድ እርምጃ በአንድ ዓይነት መስተናገድ አለበት። ት/ቤቶች ስለ ማስጨነቅ፣ ወከባ፣ እና ማስፈራራት፣ በንቃት መከታተል እና መፍትሔ መስጠት አለባቸው።
- የፆታ ለውጥ ያደረጉ ተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ በየት/ቤታቸው የፆታ ለውጥ ያደረጉ እና ሥርዓተ ፆታ የማያሟሉ/የማያሳዩ ተማሪዎች ተረጋግተው ለመማር እንዲችሉ አግባብ ያለው እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለባቸው።
- በነባራዊ ወይም በይሆናል ግምት በፆታቸው ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪዎች መቀጣት አይገባቸውም።

ሰላማዊ ስፍራ

- መተላለፊያ/ኮሪዶር ወይም "ውልብ" ብሎ የሚታለፍበት አስፈላጊ ከሆነ፣ ፆታ የቀየሩ ወይም ሥርዓተ -ፆታ የማያሟሉ ተማሪዎች ችግር የሚያጋጥመው/የሚያጋጥማት መስሎ ከታየው/ከታያት ወደ ሰላማዊ ቦታ (ለምሳሌ፡- ዋናው ቢሮ፣ ካውንስለር ቢሮ) እንዲሄዱ ት/ቤቶች መፍቀድ አለባቸው።
- ሰላማዊ ክልል፡- ት/ቤቶች ከመምህራን ማስተማሪያ ክፍሎች የተወሰኑትን፣ የተወሰኑ ቢሮዎችን፣ ወይም በት/ቤት ውስጥ የተወሰነ ስፍራ ሰላማዊ አካባቢ የሆነ ቦታ፣ ማንኛውም ተማሪ፣በማናቸውም ምክንያት ከትችትና ማንጓጠጥ ነፃ ሆነው መቆየት የሚችሉበት ስፍራ ለይተው መመደብ አለባቸው።

ክለሳ የተደረገበት ቀን፡- 8/11/17